የኢትዮጵያ
ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL (EHRCO)

## ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን አስመልክቶ ከኢሰመጉ የተሰጠ መግለጫ

**የካቲት 29/2015ዓ.ም**

### መግቢያ፡

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በአውሮፓ እና በአሜሪካ በሚገኙ አገራት በነበሩ የሴቶች እንቅስቃሴዎች እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1911 ጀምሮ በአለም አቀፍ ሁኔታ ሲከበር የቆየ በዓል ነው፡፡ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በያዝነው ዓመትም ለ112ኛ ጊዜ የሚከበር ሲሆን ይህ በዓል መከበር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ በርካታ የታሪክ ውጣ ውረዶችን ያሳለፈ ነው፡፡ ይህ በዓል እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1975 ጀምሮ በተባበሩት መንግስታት አማካኝነት በደማቁ ሲከበር ቆይቷል፡፡ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በየዓመቱ የተለያዩ መሪ ቃሎችን በመያዝ የሚከበር ሲሆን በአለም አቀፍ ደረጃ "Embracing Equality" እኩልነትን መቀበል በሚር መሪቃል የሚከበር ሲሆን በሀገራችንም ‹‹እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ›› በሚል መሪ ቃል ለ 47ኛ ጊዜ ይከበራል፡፡

### የሴቶች መብቶች አሁናዊ ሁኔታ

በአገራችን ኢትዮጵያ በያዝነው 2015 ዓ.ም እንዲሁም ባሳለፍነው 2014 ዓ.ም ዘርፈ ብዙ የሆኑ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በሴቶች ላይ ተፈጽመዋል፡፡ ሴቶች በመኖሪያ ቤታቸው፣ በሚማሩበት ትምህርት ቤት፣ በመስሪያ ቤታቸው፣ በመኖሪያ አካባቢያቸው እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች ላይ ለተለያዩ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንዲሁም ለወሲባዊ ጥቃቶች ተጋልጠዋል፡፡ ይህ ጥቃት የሴቶችን ዘር፣ ሀይማኖት፣ ቋንቋ፣ አመለካከት እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊ መደቦችን ሳይለይ በየትኛውም እድሜ ክልል ውስጥ ባሉ ሴቶች ላይ ተፈጽሟል፡፡ ሴቶች ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች በመሆናቸው ተገቢው የሆነ ጥበቃ እና ከለላ ሳይደረግላቸው በመቅረቱ ለበርካታ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋልጠዋል፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ በሚነሱ ግጭቶች ምክንያት በርካታ ቁጥር ያላቸው ሴቶች ተፈናቅለዋል፣ በረሀብ እንዲሁም በተደጋጋሚ በሚነሱ ድርቆች ምክንያት በርካታ ሴቶች ልጆቻቸውን ጨምሮ ለከፍተኛ ችግር ተጋልጠዋል፣ ሴቶች በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ በእኩልነት እንዲሳተፉ ባለመደረጉ ምክንያት በርካታ ቁጥር ያላቸው ሴቶች በኢኮኖሚያዊ ጥገኝነታቸው ምክንያት ለተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ እንዲሆኑ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን ድምጻቸውን አውጥተው ለመብታቸው እንዳይታገሉ ከፍተኛ ተጽእኖን ፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም በአገራችን ኢትዮጵያ የሴቶች የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎችም መስኮች ላይ ያላቸው ተሳትፎ መሻሻሎችን ያሳየ ቢሆንም አሁንም ድረስ ሴቶች ውሳኔ ሰጪነት ቦታዎች ላይ ያላቸው ተሳትፎ አነስተኛ በመሆኑ በቂ እና ተገቢ የሆነ የሴቶች ተሳትፎ እንዳይኖር እንዲሁም ለሴቶች ጉዳይ

ትኩረት እንደይሰጠው ከፍተኛ መሰናክል ሆኗል፡፡

**የኢሰመጉ ጥሪ፡**

ኢሰመጉ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንኳን ለዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በሰላም አደረሳችሁ እያለ የሴቶችን እኩልነት ከመቀበል ባለፈ ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ አንዱ የሰብዓዊ መብት መከበር መገለጫ መሆኑን ኢሰመጉ ያምናል፡፡

- ኢሰመጉ አገራችን ኢትዮጵያ ሴቶችን እኩልነት ከቃል ባለፈ በተግባር የምትቀበል እና የምታሳይ አገር እንድትሆን፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በሴቶች እኩልነት የሚያምን ህዝብ እንዲሆን፣ በዓለም አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ እና በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የሴቶች እኩልነትን የሚመለከቱ መብቶች የሚከበሩባት እና የሚተገበሩባት አገር እንድትሆን፣ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እና ወሲባዊ ጥቃቶች የሚቆሙባት አገር በመሆን ሴቶች በነጻነት ደህንነት ተሰምቷቸው እኩልነታቸው ተረጋግጦ በተለያዩ የማህበራዊ ክንዋኔዎች ውስጥ በንቃት የሚሳተፉባት አገር እንድትሆን፣
- ጾታዊጥቃትን፣ ጾታዊ እኩልነትን እና በአጠቃላይ ሴቶችን መሰረት ያደረጉ ህግጋቶች የተሸሻሉባት ኢትዮጵያን ማየት የምንጊዜም ምኞቱ መሆኑን እየገለጸ መንግስት ሴቶችን በእኩል ደረጃ አካትቶ የሚይዙ የህግ ማዕቀፎችን፣ የፖሊሲ እቅዶችን እንዲሁም መዋቅራዊ አሰራሮችን በመተግበር የሴቶችን እኩልነት በተግባር እንዲያረጋግጥ እንዲሁም በውሳኔ ሰጪነት ላይ ሴቶች ያላቸውን ተሳትፎ እንዲያጠናክር ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡
- በመጨረሻም መንግስት፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ የመገናኛ ብዙሀን፣ ሲቪክ ማህበራት እና ባለድርሻ አካላት ለጾታዊ እኩልነት መረጋገጥ እና ጾታዊ እኩልነትን የሚቀበል ማህበረሰብ በመገንባት ረገድ የበኩላቸውን እንዲወጡ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ